የጌታ መሢሕ

“☞ #በጌታም_የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር☜።”

— ሉቃስ 2፥26

"መሢሕ" - የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን "የተቀባ" ማለት ነው።መሢሕ በግሪኩ "ክርስቶስ" ነው።እስራኤላውያን ከጥንት ጀምሮ አምላካቸው እንደሚልከላቸው ተስፋ የሰጣቸውን መሢሕ(ቅቡዕ) ሲጠባበቁ እንደኖሩ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ያመለክታሉ(ዮሐ 4;35፣ሉቃ 3;15፣ዮሐ 7;31)።መሢሑ በብሉይ ኪዳን የተቀቡ ሰዎች ለሚሰጧቸው ሶስት አገልግሎቶች የተቀባ እንደሆነ እንመለከታለን፤ እነዚህም ለንግስና፣ ለነቢይነትና ለክህነት አገልግሎት ናቸው።ኢየሱስም ለንግስና(ሉቃ 1;33)፣ ለነቢይነት(ማቴ 13;57፣ዮሐ 6;54) እና ለክህነት(ዕብራ 5;5) አገልግሎት የተለየ ቅቡዕ ነው።እግዚአብሔር ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስና በሀይል እንደቀባው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል(ሐዋ 10;38)።

በአይሁድ ዘንድ መሢሑ የሚጠራበት ሌላኛው መጠሪያ "የዳዊት ልጅ" የሚለው ሲሆን ይህም መሢሑ የሚመጣው ከዳዊት ዘር እንደሆነ እግዚአብሔር ለዳዊት ከገባለት ኪዳን በመነሳት የተሰጠው ስም ነው(መዝ 132;11)።የክርስቶስን ንግስና የሚያነላው የማቴዎስ ወንጌልም "የዳዊት ልጅ" በማለት መጽሐፉን የጀመረው ከዚህ የተነሳ ነው(ማቴ 1;1)።በአንዳንድ ስፍራዎች "የቡሩክ ልጅ"(ማር 14;61) ፣ "ወደ አለም የሚመጣው ነቢይ"(ዮሐ6;14) እና "በጌታ ስም የሚመጣ"(ማር 11;9) በሚል አይሁድ ሲጠሩት እንመለከታለን።" የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለው መጠሪያም "ክርስቶስ" ከሚለው ጋር ብዙ ጊዜ በአንድ ላይ ይጠራል(ማቴ 26;63፣ዮሐ 1;50)።

ይህ የጌታ መሢህ ዘመኑ በደረሰ ጊዜ እንደሚወለድ አስቀድሞ በተነገረለት በይሁዳ አውራጃ በቤተልሔም ተወለደ(ት.ሚክያስ 5;2፣ ማቴዎስ 2;1)፤ እርሱም ለአህዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሀንና የእስራኤል ክብር ነው።ይህ መሢሕ እግዚአብሔር ከዘላለም ለሰዎች ያሰበውን አሳብ የፈጸመበት ታላቅ መድሀኒት ነው።የዘላለምን ሕይወት ያገኘንበት ጸጋ አስቀድሞ በመሢሁ በክርስቶስ ተሰጥቶን በእርሱ መምጣት ደግሞ እንደተገለጠ መጽሐፍ ይናገራል(2ጢሞ 1;9-11)።ይህ መሢህ የአህዛብ ብርሀን በመሆኑ ከኪዳን ርቀው የነበሩትን አህዛብ ወደ እግዚአብሔር ያቀረበ ነው(ኤፌ 2;13)፤ በዳዊት ዙፋን ላይ በመንገስ የእስራኤልን ተስፋ የሚፈጽምበት ዘመን ደግሞ ወደፊት ይመጣል(ዳን 2;44)።

በመሢሑ ተስፋ የሚያደርጉ አያፍሩም(ነጴጥ 2;6)፤ መሢሑ የበረከት ምንጭ ነው፤ እርሱ ብርሀን ነው፤ እርሱ ሕይወት ነው፤ እርሱ የተስፋ ፍጻሜ ነው፤ እርሱ ጽድቅና የዘላለም ሕይወት ነው።ይህም መሢሕ ኢየሱስ ነው፤ ይህንንም ማመን የዘላለም ሕይወት ነው(1ዮሐ 5;1)።